# እንደገና !

(ከክሻፋ )

ዛሬም እንደገና ብእርህ አጉዋራ

ጥላቻን ሊዘራ

በጭፍን ሥም ማጥፋቱ

እንደ ትላንቱ አለመሰልቸቱ

እርስበርስ መፋጀቱ

መዋሸቱ ማጣጣሉ

አለማስረጃ ሀሰት መንዛቱ

እንደ ትላንቱ

በቅንነት በለዘብታ ልዩነት ሲቻል ሊፈታ

ለጥፎ ለጣጥፎ ቃላትን ቆራርጦ

አቆላልፎ

ደምፅን ከዛ ከዚህ አወላክፎ

እንካ ስላንትያ ጠብያለህ በጉዋያ

ልትነዛነዝ ከጉዋደኛ

ጠላትህ ጠላቴ ነዉ ቢጥልህ እመተዋለሁ

ቢወረዉር እመከታለሁ

ብትቆስል ብትደማም አክምኸለሁ

ብትታመም እታመማለሁ

ብሎ በተነሰዉ ጎዋድህ ላይ መነሳቱ

እምኑ ላይነዉ ዉበቱ?

ለማን ለምን ይበጂ ይሆንበጥላቻ መነፋቱ

መወጠሩ ያለነገሩ

እኩል ሳንጃ መወርወሩ

ጠላትን ከወዳጅ አለመለየቱ

መናከሱ መዋተቱ  እንዲያዉ በከንቱ

ትላንት በጉዋደኛህ ላይ የወረወርከዉ ሳንጃ

ደሙ ታጥቦ ሳይጠራ

ዛሬም እንደገና ?

ጩኸትከን በሚጮኸዉ

ብትወድቅ ደግፎ ከሚያነሳዉ

ጠላትህን ጠላቱ ካደረገዉ

በሱ ላይ ትነሳለህ ?

የትግል ሐይል ታዳክማለህ ?

ዛሬም እንደገና ጥላቻን ልትዘራ ?

ንገረኝ እስኪ እስከመቸ በጥላቻ ፖለቲካ ፍሬ ላታፈራ

በስም ማጥፋት አሉቦልታ ዳንኪራ ትረግጣለህ

እያየኸዉ እየወደቅከ ተቸንፈህ

ማንን ጎድቶ ማንን ለመጥቀም

እንካ ሥላንትያ ከጉዋድህ ጋር መግጠም

እንደና ?

ጦርነቱ ሥም ማጥፋቱ

እርስ በርስ መባላቱ

ያ አገር ሺያጩ አጥፊዉ  አፍህን የቆለፈ

እግርህን በእግር ብረት የቸነከረ ዛሬ አንተን አሰለፈ?

እህትህን ያስደፈረ ወድምህን የገደለ

ቁሞ ይስቃል አንተ እርስ በርስህ ስትብላላ

እንደገና

ይደሰታል በከንቱነትህ

በመዳፉ ዉስጥ በመዉደቅህ

በዉስጥህ አሜኬላዎች ተክሎ

የወዳጁ ጠላት አሰልፎ እንደባብ ይነድፈሀል

ከራሱ ላይ ያወርድሀል

እንደና

ጉልበትከን ያዳከምና ሁላችሁንም ይመታል

ድል አድራጊ ይሆናል

ዛሬም እንደና ካለፈዉ ጥፋትህ አልተማርክምና

አንተ በእንካ ስላንትያ በቃላት ስትጠላለፍ

ባጉል ኩራት ተወጥረህ ለመታዬት ስታሰፈስፍ

ከጉዋደኛህ ለመብለጥ ስትጥር

ድል እንዳደረገ ጀግና በስም አጥፊነት ስትወጠር

እንደገና

እዉስጥህ ይገባና

እንደነቀዝ ቦርቡሮ አሮጌ እንጨት ያደርግኸል

መሰረትህን ይነቅላል

ዛሬም እንደገና

ብዙ አትክልቴዎች ተክሎአልና በስም አጥፊዎች

በሁለት ቢላ በይዎች

ለሆድ ያደሩ ሆዳሞች

እዉስጥህ ሰግስጎአል

መሰረታዊ ልዩነት ነዉ ከቶ መቸ ይተዉሀል

ተረት ተረት ልንገርህ

ምን ተደረገ በለኛ ከረሳኸዉ ልድገምልህ

እዉስጥህ

ተሠግሥገዉ ነዉ ጎደኛህን ያስጠፉህ

አንተ ከጉዋደኛህ ጋር ቡጢ ስትጋጠም

ጥላቻ ስታመነዢክ ስታጣጥም

ከዛ አብሮ ጨኸትኸን ከጮኸ አብሮህም ከወደቀ

ስትራብ ከተራበ ስትሰደድ ከተሰደደ ራሱን ባደቀቀ

ከፋሺስት ጥይት አምልጦ

እንዳንተ ሕይወቱን ጨብጦ

ጎዋዴ ብሎ ካንተ ጋራ

ለሕይወቱ ሳይራራ

እምነትህ ከምነቱ ተጣምሮ

ላገሩ ሕዝብ ነፃነት ሊታገል ሊያሰማ እሮሮ

ያ ጉዋድህ አብሮ አደግህ እንዴት ይረሳህ ዘንድሮ ?

በሱላይ ስትነሳ እጁህ የብዕር ቃታ ሲያነሳ

ምነው ለህዝብ ለዕውነት ለመሞት የተገባው ቃል ተረሳ?

ያንግዜነዉ ቀበሮዉ ባንድ ሆኖ ተመካከሮ

በቁዋንቋዋ በዘር ተቀራርቦ በአንድ ሆኖ ተጣምሮ

አንተን ገዝግዞ አሰልስሎ የበተነህ የመታህ

እንዳትነሳ ያደረገህ

ዛሬም እንደገና

ጩኸትህን በሚጮኸዉ አሻፈረኝ ባለዉ ላይ ተነስተህ

ስሙን ሰባዓዊነቱን ታጠፋልህ

ምን አገኘህ ?

ማን ነዉ ተጠቃሚዉ በዚህ የሞኞች ጨዋታ

የአንድ ሰኮንድ ዋካታ

ማን አሸናፊ ይሆናል

ማንስ ወድቆ ይረታል

አገር ወገን ምን ያገኛል?

ትግሉን ምን ያህል ያራምዳል ?

ላምባገነን መሳቂያ ከመሆን በቀር ከዚህ ከቶምን ይገኛል?

ሞኝነትህ ያስቀኛል

ለግል ነዉ ወይስ ላገር

ያንተ በትግል ሥም መግደርደር

እኔማ እንደና

ያንተን ከንቱ ዉዳሴ አልሰማ

የሰዉን ሀሳብ መቃወም በርግጥ ማስረጃ አቅርቦ

ትግሉን ለማፋጠን መላምት አንግቦ

ተገቢ ነበር እኮ

እንደና

እንደ አምባገነኖቹ እኔ ያልኩት ካልሆነ ብለህ

አገናዝቦ ተንትኖ ተቃዉሞ መፃፍ ሲያቅትህ

የታብሎይድ አይነት ዘመቻ

በጂምላዉ ሥም ማጥፋት ብቻ

እንደገና ? ማን አንተን ሲሰማ

ሁሉንም ስትናደፍ

በቁጣ አለንጋ ስትገርፍ

ጠላት አበዛህ ብቻህን ቀረህ

በከንቱ ዉዳሴ ተሞልተህ

የትላንት ጓድህን በሀሳብ ልዩነት ብቻ

በጎራዴ ካረድከዉ

ካገር አጥፊ አምባነን ለይተህ ካላየኸዉ

አንተም በትንሽዋ ቤት ዉስጥ

አንባገነን ነዉ የሆንከዉ

እኔማ የመሰለኝ

ድሮ ድሮ ስንገኛኝ

የሰዉ መብት እንዲከበር

የፈለገዉን እንዲናገር

እንዲፅፍ እንዲደሰኩር

ያሰኘዉን እንዲከተል

ደግፎም እንዲለፍፍ ተቃዉሞም እንዲመሰክር

ባገሩም እንዲኮራ

በቤቱም እንዲሆን አዉራ

ለዛ ነበር እኮ ትግላችን ዲሞክራሲን ለማስከበር

ባንድ ቁመን ተሰልፈን በፍቅር

ተቻችለን ተመሳጥረን ለትግሉ ልንወድቅ ተማምለን

ብዙ አሳለፍን ተባብረን

ታድያ እንደና

ሲመታ በገና ለሥም ማጥፋት ዘመቻ

በጎዋድ ላይ ጥላቻ

የታጋይን ቅስም ለመስበር

አፍ ለማዘጋት ለማሳፈር

ከሆነ የተነሳኸዉ አምባገነኖችን ለማስደሰት

ታጋዮችን ለመበተን ስም ለማጥፋት ባሰት

ዉስጣቸዉን በመሸርሸር

መብታቸዉን በመድፈር

ግፈኞችን ለማስደሰት ጓዶችን ለማሳፈር

እነሱንም በመከተል ዛሬም እንደገና እዉስጣችን ግባና

እርስ በርሳችን አፋጀና?

አመፀኛ አትመስለኝም፣ አመፀኞችን ከከዳህ

ባላማቸዉ ላይ ሳይሆን ስማቸዉ ላይ ካተኮርክ

እንደገና እንደጥንቱ ሥም ማጥፋቱ ላይ ከተሰለፍክ፣

ወዳጅና ጠላትክን ለይተህ መምታት ካልቻልክ

ፍፁም ካለፈዉ ያልተማርክ

አዉቆ አጥፊ ትሆናለህ

ለጠላትም ትጠቅማለህ

ሸማ እንደረድፉ ይለበሳል ተብሎአል

ጠላትና ወዳጄን በአንድ ቀላህ ከመታህ

አንተም ያገርና የታጋይ ጠላት ትሆናለህ

የብዕርህ ቀለም ጥላቻን በታጋይዎች ላይ ሲነፋ

አብሬህም አልደነፋ

ካንተ ጋራ

እንደገና !!